# <u>አምናና ዘንድሮ</u>

ዛሬን ሳስታውሰው ፣ ይረበሻል ቀልቤ

ምናለ እንደ ትላንት ፣ ቢሆን ይላል ልቤ

ሰዉም እንደትላንት ፣ ቅን ቢሆን ምናለ

የዘንድሮን ትቶ ፣ አምናን ባስተዋለ

ትላንት እና ዛሬ ፣ አምናና ዘንድሮ

አንደኛው ካንዱ ጋር ፣ ዘመን ተወዳድሮ

ትላትና እና አምና ፣ በለጠ እንደወትሮ

ተሸንፎ ወጣ ፣ ዛሬና ዘንድሮ

ዘንድሮና ዛሬ ፣ በሚሰራው አፍሮ

እንዳምና ካቻምና ፣ በኖረ ተከብሮ ።

ታዛቢው

September 3/2009